የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሶስተኛ ዓመት ቁጥር ፺፫
አዲስ አበባ መስከረም ፭ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No.93
ADDIS ABABA, 15st September 2017

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፬፻፲፯/፪ሺ፱

የኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

…………………………………………..ገፅ ፱ሺ፱፻፲፭

CONTENT

Regulation No 417/2017

Industrial Parks Council of Ministers Regulation

………………..............................page 9915

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፲፯/፪ሺ፱**

## ስለኢንዱስትሪ ፓርኮች የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፰ አንቀጽ ፭ እና በኢንዱስትሪ ፓርኮች አዋጅ ቁጥር ፰፻፹፮/፪ሺ፯ አንቀጽ ፴፪(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩.አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፲፯/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪.ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፤

፩/ "አዋጅ" ማለት የኢንዱስትሪ ፓርኮች አዋጅ ቁጥር ፰፻፹፮/፪ሺ፯ ነው፤

፪/ "ኢንቨስትመንት አዋጅ" ማለት የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፯፻፷፱/፪ሺ፬ (እንደተሻሻለ) ነው፤

፫/ "ቦርድ" ማለት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ ነው፤

፬/ "ኮሚሽን" ማለት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ነው፤

**Council of Ministers Regulation No 417/2017**

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION ON INDUSTRIAL PARKS

This Regulation is issued by the Council of Minister pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916/2015 and Article 32(1) of the Industrial Parks Proclamation No. 886/2015.

## SECTION ONE
## GENERAL

### 1.Short Title

This Regulation may be cited as the "Industrial Parks Council of Ministers Regulations No. 417/2017".

### 2.Definitions

In this Regulation, unless the context otherwise requires:

1/ "Proclamation" means the Industrial Parks Proclamation No. 886/2015;

2/ "Investment Proclamation" means the Investment Proclamation No. 769/2012, (as amended);

3/ "Board" means the Ethiopian Investment Board;

4/ "Commission" means the Ethiopian Investment Commission;



www.chilot.me

፭/ "ኮርፖሬሽን" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፳፮/፪ሺ፮ የተቋቋመው የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ነው፤

፮/ "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው፤

፯/ "የስሪት አገር የምስክር ወረቀት" ማለት አንድ ዕቃ ስለተመረተበት አገር ትክክለኛነት በተመረተበት አገር ሥልጣን ባለው አካል የሚሰጥ የማረጋገጫ ሰነድ ነው፤

፰/ "የኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚ" ማለት ማንኛውም የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ፣ አስተዳዳሪ፣ ድርጅት፣ ሠራተኛ ወይም ነዋሪ ነው፤

፱/ "የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት" ማለት የጉምሩክ ሕግን ለማክበርና ለማስከበር በሚመለከታቸው ሰዎችና በባለሥልጣኑ የሚከናወኑ የጉምሩክ ሂደቶችን ያጠቃልላል፤

፲/ "የጉምሩክ ቁጥጥር" ማለት የጉምሩክ ሕግ መከበሩን ለማረጋገጥ በባለሥልጣኑ የሚወሰድ ማንኛውንም ሕጋዊ እርምጃ ነው፤

፲፩/ "መሠረተ-ልማት" ማለት በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ መብራት፣ ውሃ፣ የቴሌኮም (የድምጽ፣ የዳታ፣ የቪዲዮና ተዛማጅ አገልግሎቶች)፣ ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ እና የአየር ብክለት መቀነሻ ሥርዓት ማሟላት እንዲሁም በፓርክ ውስጥ የሚከናወኑ የመንገድና ሌሎች አስፈላጊ ግንባታዎችን ያካትታል፤

፲፪/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፮) የተሰጡት ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በዚህ ደንብ የተካተቱት ሌሎች ቃላት ወይም አገላለጾች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይይዛሉ፤

፲፫/ በማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸውድንጋጌ የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

**፫.<u>የቦርዱ ዋና ዋና ተግባራት</u>**

ቦርዱ አዋጁንና ይህንን ደንብ ለማስፈጸም የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩/ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት፣ አስተዳደርና አመራር፣ ተቋማዊ ግንባታና ቁጥጥርን በበላይነት የመምራት፤

፪/ የኢንዱስትሪ ፓርክ የመሰየም፣ የተሰየመ የኢንዱስሪ ፓርክን የማሻሻል እና የመሰረዝ፤

፫/ የኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚዎችን የሚመለከቱ የፖሊሲ ጉዳዮችን የመወሰን፣ አፈጻጸማቸውን የመከታተል፤

፬/ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን በተመለከተ በሚመለከታቸው መንግሥታዊ ተቋማት የትብብርና የቅንጅት ዘላቂ ሥርዓት መዘርጋቱን የማረጋገጥ፤

5/ "Corporation" means the Industrial Parks Development Corporation established pursuant to the Council of Ministers Regulation No. 326/2014;

6/ "Authority" means the Ethiopian Revenues and Customs Authority;

7/ "Certificate of Origin" means a document issued by a competent authority in the country of production certifying the authenticity of the origin of goods;

8/ "Industrial Park End-User" means any industrial park developer, operator, enterprise, employee or resident;

9/ "Customs Procedure" includes all customs operations carried out by the persons concerned and the Authority in order to ensure compliance with customs law;

10/ "Customs Control" means any lawful measure applied by the Authority to ensure compliance with customs law;

11/ "Infrastructure" means provision of electricity, water, telecom including voice, video, data and other related services, installation of a system for the disposal of solid waste, liquid waste and reduction of air pollution in an industrial park and includes construction of roads and other necessary structures within a park;

12/ without prejudice to the definitions provided under sub-articles (1) to (6) of this Article, other terms and expressions used in these Regulations shall have the meaning attributed to them in the definitional provisions of the Proclamation;

13/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

**3. <u>Main Duties of the Board</u>**

The Board, with the view to implementing the Proclamation and this Regulation, shall have the following main duties:

1/ provide high-level guidance for the development, operation, and management of industrial parks and institution building and control;

2/ designate industrial parks, make amendments to and cancel the designation;

3/ decide on policy matters regarding industrial park end-users and follow up the implementation of its decisions;

4/ ensure that the concerned government organs, through cooperation and coordination, put in place a sustainable system as regards one-stop shop service;

5/ adopt strategies and studies that enable to create and

፭/ በፓርኮች ውስጥ የእውቀትና የክህሎት ሽግግር መኖሩን ማረጋገጥ፣ እንዲሁም የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ወደ ፓርኮች በመሳብ፣ በመመልመልና በመደገፍ ዘርፈ-ብዙና ቀጣይነት ያላቸው የግብዓት ትስስሮች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ እንዲፈጠሩ በዘርፉ አዲስ የምርት አቅም እንዲስፋፉ የሚረዱ ስትራቴጂዎችና ጥናቶችን የማጽደቅ፣

፮/ ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ቅሬታዎችን ለማስተናገድ ደረጃውን የጠበቀ የቅሬታ ማስተናገጃ ሥርዓት መዘርጋቱን የማረጋገጥ፡፡

## ፬. የኮሚሽኑ ዋና ዋና ተግባራት

ኮሚሽኑ አዋጁንና ይህንን ደንብ ለማስፈጸም የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩/ በኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚነት ሊሰማሩ የሚችሉ ብቃት ያላቸው ባለሀብቶችን የመመልመል፣

፪/ በኢንዱስትሪ ፓርክ አምራችነት ሊሳተፉ የሚችሉ ብቃት ያላቸውን የአገር ውስጥ እና የውጭ አገር ባለሀብቶችን በመመልመልና ስምምነቶችን በመፈጸም ፓርኮች ሙሉ በሙሉ በአምራች ድርጅቶች መያዛቸውን የማረጋገጥ፣

፫/ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚገኙ የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅቶች በተሳለጠ ሁኔታ የአንድ ማዕከል አገልግሎት እያገኙ መሆናቸውን የማረጋገጥ፣

፬/ ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ጋር በተያያዘ የእውቀት እና የክህሎት ሽግግር የሚያመጡ፣ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ወደ ፓርክ በመሳብና በመደገፍ ዘርፈ-ብዙና ቀጣይነት ያላቸው የግብዓት ትስስሮች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ እንዲፈጠሩና በየዘርፉ አዲስ የምርት አቅም እንዲስፋፉ የሚረዱ ስትራቴጂዎችና ጥናቶችን ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር በመመካከር ነድፎ በቦርዱ በማጸደቅ ተግባራዊ የማድረግ፣

፭/ ለኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅቶች የሎጅስቲክስና የኤክስፖርት ድጋፍ የመስጠት፣

፮/ ለኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚሆን መሬት መዘጋጀቱንና መሰየሙን የማረጋገጥ፣ የሊዝ፣ የንዑስ-ሊዝና የግንባታ ፈቃዶች በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት መሰጠታቸውን የማረጋገጥ፣ መሠረተ-ልማት በአግባቡ መቅረቡን፣ በዕቅዱ መሠረት መልማቱን እንዲሁም ለምርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች ሥራ ላይ መዋሉን የማረጋገጥ፣

፯/ የኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚዎች መብትና ግዴታ መከበራቸውን የማረጋገጥ፣

፰/ የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅቶች፣ አልሚዎች ወይም አስተዳዳሪዎች ሕጋዊ ሰውነት አግኝተው እንደ አመቺነቱም በተደራጀ መልክ ከመንግሥት ጋር ቀጣይነት ያለው ምክክር እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን የማመቻቸት፣

expand new productive capacity, as well as attract and recruit domestic investors to industrial parks, support them, create multi-faceted, sustainable inter-linkages of inputs, and ensure transfer of knowledge and skill within parks;

6/ ensure that a suitable complaint handling mechanism is put in place to resolve dispute arsing in relation to industrial parks.

## 4. Main Duties of the Commission

The Commission, with the view to implementing the Proclamation and these Regulations, shall have the following main duties:

1/ recruit suitable investors that can engage in the development of industrial parks;

2/ recruit suitable domestic and foreign investors that can engage in the manufacturing sector, conclude agreements with them and ensure full occupancy of industrial parks by manufacturing enterprises;

3/ ensure that industrial park enterprises get streamlined one-stop shop service within the industrial parks;

4/ develop in consultation with the Ministry of Industry and facilitate adoption by the Board of strategies and studies that help create and expand new productive capacity, attract and support domestic investors to industrial parks, create multi-faceted, sustainable inter-linkages of inputs, and ensure transfer of knowledge and skill within parks and implement such strategies once adopted;

5/ provide to industrial park enterprises logistical and export support;

6/ ascertain that land is prepared and designated as industrial park; ensure lease and sub-lease agreements are concluded, construction permits are granted in accordance with the system in place; ensure that infrastructure is developed as per the plans, provided properly and utilised for production and provision of associated services;

7/ ensure that the rights of industrial park end-users are respected and their obligations discharged;

8/ facilitate conditions necessary for industrial park enterprises, industrial park developers or operators to gain legal personality and to engage with the Government, as the case may be, organised continuous dialogues;

www.chilot.me

፱/ የኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚዎችን የሚመለከቱ የፖሊሲ ጉዳዮችን በጥናት በመለየት በቦርዱ የማስወሰንና የማስፈጸም፤

፲/ ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ጋር በተያያዘ በሚመለከታቸው አካላት የሚያካሄድ የሠራተኞች ምልመላና ሥልጠና የማስተባበር፣ለኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅቶች የማህበረሰብ ሬድዮ ስርጭትን ጨምሮ ሌሎች የተለያዩ የተግባቦት ዘዴዎችን በመጠቀም በፋብሪካ ደረጃ ሠራተኞች ለሥራ ያላቸው ተነሳሽነት እንዲጨምር የማገዝ፤

፲፩/ ስለኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚዎች የመሬት ልማትና የግንባታ አፈጻጸም፣ የፋብሪካና ሌሎች ሕንጻዎች አጠቃቀም፣ የምርትና የወጪ ንግድ አፈጻጸም፣ የአገር ውስጥና የውጭ አገር ሠራተኞች የቅጥር ሁኔታ፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎት አፈጻጸምና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን አጠናቅሮ የያዘና የተተነተነ ወቅታዊ ሪፖርት ለቦርዱና ለሌሎች አግባብነት ላላቸው አካላት የማቅረብ፡፡

## ክፍል ሁለት
## የኢንዱስትሪ ፓርክ አሰያየምና የኢንቨስትመንት ፈቃድ

### ፭. ስለኢንዱስትሪ ፓርክ አሰያየም

፩/ ኮርፖሬሽኑ ወይም ሌላ የኢንዱስትሪ ፓርክ ለማልማት የሚፈልግ ማንኛውም ባለሀብት አንድን የለማ ወይም ያልለማ ቦታ የኢንዱስትሪ ፓርክ ተብሎ እንዲሰየምለት ለኮሚሽኑ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፡፡

፪/የኢንዱስትሪ ፓርክ አሰያየም ማመልከቻ የአዋጁን አንቀጽ ፳፭ (፪) ድንጋጌ ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡

፫/የኢንዱስትሪ ፓርክ አሰያየም ማመልከቻው በአዋጁ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዋናነት የሚከተሉት መኖራቸውን ማሳየት ይኖርበታል፤

ሀ) ለዜጎች የሥራ ዕድል፤

ለ) የዕውቀት፣ የክህሎት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር፤

ሐ) ኤክስፖርትን የማሳደግ አቅም፤

መ) የግብዓት አቅርቦትና ትስስር፤

ሠ) አገራዊና ክልላዊ የመሠረተ-ልማት እድገት፤

ረ) ለኢንዱስትሪ ፓርክ አስፈላጊ የሆነ የሰው ኃይል አቅርቦት፡፡

፬/ በኢንዱስትሪ ፓርክነት የሚሰየመው አነስተኛ የመሬት መጠን እንደ ፕሮጀክቱ ሁኔታ እየታየ በቦርዱ ይወሰናል፡፡

9/ conduct studies to identify policy issues of relevance to industrial park end-users, submit and cause decision of the Board and implement same;

10/ coordinate the responsibilities of relevant bodies with regard to recruitment and training of industrial park workforce, and enhance work morale of workers of industrial park enterprises at plant-level by making use of community radio transmission and other means of communication;

11/ submit to the Board and other relevant bodies up-to-date reports containing necessary data and analysis bout industrial park end-users land development and construction performance, utilisation of factory and other buildings, manufacturing and export trade performance, employment status of domestic and foreign workers, one-stop shop service delivery and other important information.

## SECTION TWO
## DESIGNATION OF INDUSRIAL PARK AND INVESTMENT PERMIT

### 5 .Designation of an Industrial Park

1/ The Corporation or any other investor that wants to develop an industrial park shall apply to the Commission for the designation of an undeveloped or a developed land as an industrial park.

2/ The application for designation shall consider the provision of Article 25(2) the Proclamation.

3/ Without prejudice to the provision of the Proclamation and sub-article (2) of this Article, the application for the designation of an industrial park shall demonstrate the following:

a) creation of job opportunities for citizens;

b) transfer of knowledge, skill and technology;

c) potential to increase export;

d) backward and forward linkages of input;

e) contribution to national and regional infrastructure development and

f) Availability of human resource necessary for an industrial park.

4/ The Board may determine the minimum size of land to be designated as an industrial park in light of the peculiarities of each project.

www.chilot.me

፭/ በኢንዱስትሪ ፓርክ ቅጥር ግቢ ውስጥ ለፋብሪካ፣ ለጋራ መጠቀሚያ፣ ለመኖሪያ እና ተያያዥ ሕንጻዎች እንዲሁም ለመሠረተ-ልማት የሚውለው መሬት ከጠቅላላ ይዞታው ከ፶ በመቶ ማነስና ከ፸፭ በመቶ መብለጥ የለበትም፤ ሆኖም ቦርዱ ለእርሻም ይሁን ለግጦሽ ሊውል የማይችል መሬት ለአካባቢ ጥበቃ በሚረዳ መልኩ በኢንዱስትሪ ፓርክነት እንዲለማ ጥያቄ ከቀረበና ካመነበት ከዚህ በተለየ ሁኔታ ሊወስን ይችላል፡፡

፮/ ኮሚሽኑ የአሰያየም ማመልከቻውን መርምሮ የውሳኔ ሀሳቡን በሰላሳ ቀናት ለቦርዱ ያቀርባል፡፡

፯/ ቦርዱ ከኮሚሽኑ በሚቀርብ የውሳኔ ሀሳብ መሠረት በኢንዱስትሪ ፓርክነት የተሰየመን መሬት መጠንና የሚተላለፍበትን የሊዝ ዋጋ በመወሰን ለተመረጠው አልሚ እንዲተላለፍ ይወስናል፡፡

፰/ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ግንባታ ከመጀመሩ በፊት ለኮሚሽኑ የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) የኢኮኖሚ አዋጭነት ጥናት፣ የኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት ፕላንና የሀይድሮሎጂ ጥናት ሰነድ፤

ለ) የፋይናንስ አቅም የሚያሳይ ማስረጃ፤ እና

ሐ) የአካባቢና የማሕበራዊ ተጽእኖ ግምገማ ሪፖርት ጋር በተያያዘ ፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንዲሆን በሚመለከተው መንግሥታዊ ተቋም ይሁንታ የተሰጠው መሆኑን የሚገልጽ ደብዳቤ፡፡

፱/ ኮሚሽኑ የቦርዱን ውሳኔ በተወሰነ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

## ፮.ልዩ የኢንዱስትሪ ፓርክ አሰያየም

፩/ ቦርዱ እንደ አስፈላጊነቱ አንድን የኢንዱስትሪ ፓርክ የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት፣ የተቀናጀ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ፣ የቴክኖሎጂ፣ የፋርማሲዩቲካል፣ የብረታ ብረት ወይም ሌላ የተለየ ባህርይ ያለው ልዩ የኢንዱስትሪ ፓርክ ብሎ ሊሰየም ይችላል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ አንድን ቦታ ከባለሥልጣኑ ጋር በመመካከር ዕቃዎች የሚራገፉበት፣ የሚስተናገዱበት፣ የሚመረቱበት ወይም የሚገጣጠሙበት እና ወደ ውጭ እንደገና የሚላኩበት ወይም ለኢንዱስትሪ ፓርክ በግብዓትነት እንዲቀርቡ የሚደረግበት እንደ ነፃ የንግድ ፓርክና የኤክስፖርት ማቀነባበሪያ ዞን አድርጎ ሊሰይም ይችላል፡፡

5/ The land to be used for factory building, facilities for common use, infrastructure, residence and related buildings within the industrial parks area shall neither be less than 50 per cent nor exceed 75 percent of the land under possession; provided, however, that the Board may decide otherwise, in ways that conserve the environment, where an application is submitted to develop into an industrial park land that is suitable neither for agriculture nor for pasture.

6/ The Commission shall asses the application for designation and submit its recommendation to the Board within thirty days.

7/ The Board shall, based on the recommendation of the Commission, determine the size of land designated as an industrial park and its lease price and decide that the same be transferred to the selected industrial park developer.

8/ An industrial park developer shall submit the following documents before commencing construction:

a) an economic feasibility study document prepared by the industrial park developer; a park development plan and hydrological study;

b) evidence of financial capacity;

c) Letters from pertinent governmental institutions indicating the social and environmental impact assessment reports of the project have been considered and giving their go ahead for the project.

9/ The Commission shall notify the applicant in writing of the Board's decision within seven official working days.

## 6 .Designation of a Specialised Industrial Park

1/ The Board may, where appropriate, designate an industrial park as specialising in textile and apparel, integrated agro-processing, technology, pharmaceuticals, metalworking or any other specialised field.

2/ Without prejudice to sub-article (1) of this Article, the Board may designate an area as a free trade park or export processing zone in which goods may be landed, handled, manufactured or reconfigured, and re-exported or supplied as input for industrial parks in consultation with the Authority.

www.chilot.me

፫/ የልዩ ኢንዱስትሪ ፓርክ አሰያየም ማመልከቻ በኮሚሽኑ ወይም በኮርፖሬሽኑ ወይም በሌላ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ሊቀርብ ይችላል፡፡

፬/የዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣የልዩ አሰያየም ማመልከቻ የሚከተሉትን መረጃዎች በግልጽ ማሳየት ይኖርበታል፤

ሀ)እንደዚህ ያለው ልዩ ስያሜ የክልሉን ወይም የአካባቢውን የተለየ የልማት ዓላማ ለማሳካት የሚረዳ መሆኑን፤

ለ)በፓርኩ ውስጥ የሚገኙ ድርጅቶች በእርስ በርስ ትስስር የተሻለ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያለውን ጠቀሜታ፤ እና

ሐ)የተመረጠው አካባቢ ለግብዓት አቅርቦት ያለውን ምቹነት፡፡

፭/ ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፬) መሠረት ልዩ ስያሜ ለሰጠው የኢንዱስትሪ ፓርክ የተለየ ማበረታቻ ሊሰጥ ይችላል፡፡

**፯ .የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ የኢንቨስትመንት ፈቃድ**

፩/ ማንኛውም የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ባለሀብት የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ለመሆን ለኮሚሽኑ በማመልከት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

፪/ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡-

ሀ) በመንግሥት ቅድሚያ በተሰጣቸው ልዩ የኢንቨስመንት መስኮች ለሚሰማሩ የኢንዱስትሪ ፓርክ አምራች ድርጅቶች የሚሆን የኢንዱስትሪ ፓርክ ለማልማት የተስማማ፤

ለ) ለፕሮጀክቱ ማስፈጸሚያ በቂ ካፒታል ያለው፤ እና

ሐ) ሌሎች በኢንቨስትመንት ሕጉ ስለኢንቨስትመንት ፈቃድ አሰጣጥ የተጠቀሱትን መስፈርቶች፡፡

፫/ ኮሚሽኑም አመልካቹ ያቀረበውን ጥያቄ መርምሮ መስፈርቶቹን የሚያሟላ ሆኖ ሲያገኝ ከአመልካቹ ጋር የመግባቢያ ስምምነት በመፈራረም በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ ለአልሚው የኢንቨስትመንት ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

፬/ ለኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ የተሰጠው ኢንቨስትመንት ፈቃድ ፓርኩ የሚያተኩርበትን የኢንቨስትመንት መሰክ መግለጽ አለበት፡፡

**፰.የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ የኢንቨስትመንት ፈቃድ**

፩/ ማንኛውም የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ባለሀብት የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ ለመሆን ለኮሚሽኑ በማመልከት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

3/ The application for a specialised designation may be made by the Commission or the Corporation or another industrial park developer.

4/ Without prejudice to Article 5 of these Regulations, the application for a specialised designation shall clearly demonstrate the following information:

a) such a designation contributes to the attainment of special developmental goals of the region or locality;

b) the importance of such designation in enhancing competitiveness through creation of linkages among enterprises in the park;

c) the suitability of the locality chosen for the supply of input.

5/ The Board may grant special incentives to a park designated as a specialised industrial park pursuant to sub-article (1) to (4) of this Article.

**7.Investment Permit of an Industrial Park Developer**

1/ Any domestic or foreign investor shall apply to the Commission and secure an investment permit in order to become industrial park developer.

2/ Industrial park developer shall comply with the following requirements for the issuance of investment permit:

a) an undertaking is made to develop a park for use by industrial park enterprises that engage in special manufacturing sectors identified as priority by the Government;

b) the applicant demonstrates availability of sufficient capital for the implementation of the project and

c) other requirements for the issuance of investment permit provided for under the investment law.

3/Where the Commission finds the application comply the requirements, it shall conclude a memorandum of understanding with the applicant and issue an investment permit to the industrial park developer within seven official working days.

4/The investment permit issued to an industrial park developer shall indicate the investment sector on which the park focuses.

**8.Investment Permit of an Industrial Park Operate**

1/ Any domestic or foreign investor shall apply to the Commission and secure an investment permit to become an industrial park operator.

www.chilot.me

፪/ የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፦

ሀ) ተመሳሳይ ወይም ተያያዥ አገልግሎቶች መስጠቱን የሚያሳይ የሙያ እና የሥራ ልምድ ሁኔታ የሚገልጽ ዝርዝር መግለጫ ማቅረብ፣

ለ) ልምድ ያላቸው በቂ ባለሙያዎችና የፋይናንስ አቅም ያካተተ የአስተዳደር እና የፋይናንስ እቅድ፣ እና

ሐ) ሌሎች በኢንቨስትመንት ሕጉ ስለኢንቨስትመንት ፈቃድ አሰጣጥ የተጠቀሱትን መስፈርቶች፡፡

፫/ ኮሚሽኑም አመልካቹ ያቀረበውን ማመልከቻ በመመርመር መስፈርቶቹን የሚያሟላ ሆኖ ሲያገኘው በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

፬/ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ያለማውን ፓርክ ራሱ ለማስተዳደር ከፈለገ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተጠቀሱት መስፈርቶች በሟሟላት እና ማመልከቻ በማቅረብ የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪነት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማውጣት አለበት፡፡

**፱.<u>የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት የኢንቨስትመንት ፈቃድ</u>**

፩/ ማንኛውም የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ባለሀብት የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ለመሆን ለኮሚሽኑ በማመልከት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

፪/ የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፦

ሀ) ዝርዝር የፕሮጀክት ሀሳብ፣

ለ) እንደ ፕሮጀክቱ ዓይነት የኤክስፖርት ወይም የገቢ ምርት የመተካት ዕቅድ፣

ሐ) የፋይናንስ ሁኔታ መግለጫ እና የአስር ዓመት ትንበያ፣

መ) ፕሮጀክቱን በተመለከተ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሪፖርት፣ እና

ሠ) ሌሎች በኢንቨስትመንት ሕጉ ስለኢንቨስትመንት ፈቃድ አሰጣጥ የተጠቀሱትን መስፈርቶች፡፡

፫/ ኮሚሽኑም አመልካቹ ያቀረበውን ማመልከቻ በመመርመር መስፈርቱን የሚያሟላ ሆኖ ሲያገኘው በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ይሰጣል፡

2/ An industrial park operator shall comply with the following requirements for the issuance of investment permit:

a) detailed declaration demonstrating availability of professionals and possession of experience in rendering similar or related service;

b) administrative and financial plan demonstrating availability of funds and capacity to deploy sufficient experienced professionals; and

c) Other requirements for the issuance of investment permit provided for under the investment law.

3/ The Commission shall issue investment permit to the applicant within seven official working days where it finds that the application complies with the requirements.

4/ An industry park developer, who seeks to operate industrial park that he developed, shall apply for investment permit to operate the park upon complying with the requirements provided under sub-article (2) of this Article.

**9.<u>Investment Permit of an Industrial Park Enterprise</u>**

1/ Any domestic or foreign investor shall apply to the Commission and secure an investment permit in order to become an industrial park enterprise.

2/ An industrial park enterprise shall comply with the following requirements for the issuance of investment permit:

a) detailed project proposal;

b) export or import substitution plan depending on the type of the project;

c) declaration of financial standing and a ten-year forecast;

d) environmental impact assessment report and

e) Other requirements for the issuance of investment permit provided for under the investment law.

3/ The Commission shall issue investment permit to the applicant within seven official working days where it finds that the application complies with the requirements.

www.chilot.me

## ክፍል ሦስት
## መሬት ማስተላለፍ እና ግንባታ

### ፲. የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ እና ድርጅት የመሬት ሊዝ ይዞታ የምስክር ወረቀት

፩/ ኮርፖሬሽኑ በተቋቋመበት ደንብ ቁጥር ፫፻፳፮/፪ሺ፯ አንቀጽ (፭) (፪) መሠረት ራሱ የሚያለማውን ወይም ለሌሎች አልሚዎች የሚተላለፍን መሬት ከክልሎች በስምምነት እና በሳይት ፕላን ተረክቦ በመሬት ባንክነት ይይዛል፤ ስምምነቱም ኮርፖሬሽኑ ለራሱ ለማልማትም ሆነ ለሌላ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ መሬት በሊዝ ለማስተላለፍ የሚያስችለው መሆን አለበት፡፡

፪/ ኮርፖሬሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ከተረከበው መሬት ውስጥ የራሱን የኢንዱስትሪ ፓርክ ለማልማት ከፈለገ የመሬት ሊዝ ይዞታ የምስክር ወረቀት አግባብ ባለው የክልል መንግሥት ተቋም ይሰጠዋል፡፡

፫/ ኮርፖሬሽኑ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚነት ኢንቨስትመንት ፈቃድ ለተሰጠው ባለሀብት ከመሬት ባንክ መሬት በሊዝ ውል ሊያስተላልፍ ይችላል፤ ይህንን ተከትሎ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚው የሊዝ ይዞታ የምስክር ወረቀት ከኮሚሽኑ ያገኛል፤ ሆኖም ኮርፖሬሽኑ መሬቱን በሊዝ የሚያስተላልፈው ኮሚሽኑ ይህንን መሬት ለአልሚው እንዲተላለፍ ቦርዱን በቅድሚያ አስፈቅዶ ይህንኑ የቦርዱን ውሳኔ ለኮርፖሬሽኑ ሲያሳውቀው ብቻ ይሆናል፡፡

፬/ በኮርፖሬሽኑ ወይም በሌላ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ መሬት የተሰጠው የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ከኮርፖሬሽኑ ወይም ከዚሁ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ጋር የንዑስ-ሊዝ ውል ሲዋዋል፤ የንዑስ-ሊዝ ይዞታ የምስክር ወረቀት ከኮሚሽኑ ይሰጠዋል፡፡

### ፲፩. በኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ወይም ድርጅት የሚካሄድ ግንባታ

፩/ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ለኪራይ ወይም ለሽያጭ የፋብሪካ ሕንጻ ወይም በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የተፈቀደ ሌላ ግንባታ ማከናወን ሲፈልግ የግንባታ ፈቃድ ከኮሚሽኑ ማግኘት ይኖርበታል፤ ኮሚሽኑ ይህንን ተግባር ሲፈጽም አግባብ ካለው ተቋም ሙያዊ እገዛ እንደአስፈላጊነቱ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

፪/ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ የግንባታ ፈቃድ ሲጠይቅ የሚከተሉትን መስፈርቶች በግልጽ ማሳየት ይኖርበታል፤

ሀ) ከተፈቀደው ቦታ ውስጥ ለፋብሪካና ተያያዥ ግንባታ የሚውለው ቦታ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭(፭) ከተመለከተው ጋር የተጣጣመ መሆኑን፤

## SECTION THREE
## TRANSFER OF LAND AND CONSTRUCTION

### 10. Land Leasehold Certificate of Industrial Park Developer and Enterprise

1/ The Corporation shall, as provided under Article 5(2) of its establishment Regulation No. 326/2014, keep in the land bank the land that it obtains from Regions through agreement with and get a site plan to develop by it or to transfers to other industrial park developers. The agreement shall be reached to enable the Corporation to develop such land by itself or transfer the same in leasehold to another industrial park developer.

2/ With regard to the land it has received pursuant to sub-article (1) of this Article, the Corporation shall, as regards land that it seeks to develop itself, secure lease-hold certificate that enables it to do so from an appropriate regional institution.

3/ The Corporation shall transfer land in leasehold from the land bank to another industrial park developer that has secured investment permit only after the Commission notifies it of the decision of the Board to that effect. Following the conclusion of such leasehold, the industrial park developer shall get lease-hold certificate from the Commission.

4/ The Commission shall issue certificate of sub-leasehold to an industrial park enterprise that has acquired a developed industrial park land on the basis of sub-lease from the Corporation or another industrial park developer.

### 11. Construction by Industrial Park Developer or Enterprise

1/ An industrial park developer that wishes to carry out construction of a factory building or engage in any other construction permissible in a park for rent or sale shall secure a construction permit from the Commission. The Commission shall seek professional assistance from the Corporation or another appropriate institution in the course of discharging this responsibility.

2/ An application for a construction permit by an industrial park developer shall clearly show with the following requirements:

a) that the land to be used for factory building and related construction in the park complies with the requirements under Article 5 (5) of this Regulation;

www.chilot.me

ለ) በቂና ለአካል ጉዳተኛ ተደራሽ የሆነ እንደ መኖሪያ ቤት፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ቦታ፣ ስፖርት ማዕከል፣ አረንጓዴ ቦታ፣ የሕክምና አገልግሎት መስጫ የመሳሰሉ አገልግሎቶችን ያካተተ መሆኑን፤ እና

ሐ) በቂና ደረጃውን የጠበቀ የእሳት አደጋ መከላከያና መቆጣጠሪያ፣ እንደ ሲ.ሲ.ቲ.ቪ. ያሉ ለደሕንነት እና ለጉምሩክ ቁጥጥር አስፈላጊ የሆኑ ካሜራዎችና መፈተሻዎች፣ የዕቃ መጫኛና ማውረጃ ቦታ፣ የምድር ሚዛን፣ መጋዘንና ቢሮ፣ የመኪና ማቆሚያ ቦታ፣ የመጸዳጃና የፋብሪካ ዝቃጭ ፍሳሽ የሚታከምበት ዘዴ ያለው መሆኑን፡፡

፫/ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ የፕሮጀክት ግንባታ አፈጻጸም በተመለከተ ከኮሚሽኑ ጋር ስምምነት ይፈራረማል፡፡

፬/ የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት የፋብሪካና ተያያዥ ግንባታ አፈጻጸም የተመለከተ ስምምነት ከኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚው ወይም የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚው ከሚወክለው አስተዳዳሪ ጋር ይፈጽማል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) የተመለከቱትን ስምምነቶች ተከትሎ ኮሚሽኑ የግንባታ ፈቃድ እና ከግንባታ ጋር ተያያዥ የሆኑ ፈቃዶችን ይሰጣል፤ የግንባታ ወጪ ዝርዝር መርምሮ ያጸድቃል፡፡

፮/ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ወይም ድርጅት በስምምነቱ መሠረት ባከናወነው ግንባታ ላይ ለውጥ ማድረግ ሲፈልግ ስምምነቱን ከፈጸመው አካል እንደ አግባብነቱ ኮሚሽኑን ወይም የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚውን ማስፈቀድ ይኖርበታል፡፡

፯/ ኮሚሽኑ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚው ፕሮጀክት ወይም የድርጅቱ የፋብሪካና ተያያዥ ግንባታ አፈጻጸም አግባብ ባለው ሕግ መሠረት መፈጸሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤ ኮሚሽኑ ይህንን ተግባር በራሱ ባለሙያዎች ወይም በኮርፖሬሽኑ ወይም በሌላ አማካሪ ድርጅት አማካኝነት ሊያከናውን ይችላል፡፡

b) inclusion of facilities for, one stop-shop service, medical service, residential buildings, sport centre, green area, and the like sufficiently in manner accessible to persons with disability;

c) Inclusion of adequate fire prevention and fighting facilities, CCTV and similar systems necessary for security, customs control and cargo examination, parking, loading and unloading space, weighbridge, stores, offices, human and factory waste treatment facility.

3/ A industrial park developer shall conclude an agreement with the Commission regarding the implementation of the construction of its project.

4/ An industrial park enterprise shall conclude an agreement regarding the implementation of factory and related construction with the industrial park developer or an operator designated by the industrial park developer.

5/ The Commission shall grant construction permit, other permits related to construction, and examine and approve bill of quantities following the conclusion of agreements indicated under sub-articles (3) and (4) of this Article.

6/ An industrial park developer or enterprise that wishes to make changes to construction that was carried out in compliance with the agreement shall, as appropriate, seek the approval of the Commission or industrial park developer.

7/ The Commission shall oversee and ensure that the implementation of the project of the industrial park developer or factory and related construction of an enterprise conforms to the relevant laws. The Commission may discharge these regulatory responsibilities making use of its own professionals or those of the Corporation or by hiring a consulting firm.

www.chilot.me

## ክፍል አራት
## የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ፣ አስተዳዳሪና ድርጅት የኢንቨስትመንት ተግባራቸውን ስለሚያከናውኑባቸው ሁኔታዎች

### ፲፪.የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ፓርኩን የሚያለማበት ሁኔታ

የአዋጁ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ፡-

፩/ ግንባታ በሚያከናውንበት ወቅት የሠራተኞች ደሕንነት መጠበቁን እንዲሁም ለሠራተኞቹ አገልግሎት መስጫ፣ የመመገቢያና የመጸዳጃ ቤቶች፣ የመጀመሪያ የህክምና እርዳታ መስጫና ሌሎች ለሠራተኞች አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶች መሟላታቸውን የማረጋገጥ፤

፪/ በዚህ ደንብ፣ በአልሚ ኢንቨስትመንት ፈቃድና ስምምነት መሠረት የሕንጻዎችን ግንባታ፣ የመሠረተ-ልማትና የአገልግሎት ዝርጋታ ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ በወቅቱ የማጠናቀቅ፤

፫/ ፓርኩ የሚያተኩርበትን የኢንቨስትመንት ዘርፍ ያማከለ የምርት ጥራትና ሌሎች መመዘኛዎች መሟላታቸው የሚያረጋግጡ የምስክር ወረቀቶች የሚሰጡባቸው የአገልግሎት መስጫ ሕንጻ የማዘጋጀት፤

፬/ ስለፓርክ ልማት ያገኘውን ተሞክሮ ለኢትዮጵያውያን የማስተላለፍ፤

፭/ ስለሥራ አፈጻጸሙ በተለይ ስለኢንዱስትሪ ፓርኩ የመሬት ልማትና የግንባታ አፈጻጸም፣ የፋብሪካና ሌሎች ሕንጻዎች አጠቃቀም፣ በየሩብ ዓመቱ ዝርዝር ሪፖርት ለኮሚሽኑ የማቅረብኃላፊነት አለበት፡፡

### ፲፫.የኢንዱስትሪፓርክ አስተዳዳሪ ፓርኩን ስለሚያስተዳድርበት ሁኔታ

የአዋጁ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳዳሪ፡-

፩/ በኢንዱስትሪ ፓርክ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች አግባብ ባላቸው ሕጎችና ከአስተዳዳሪ ስምምነት ጋር በተጣጣመ መልኩ የመፈጸም፣

፪/ የፓርክ አስተዳደሩ ምክንያታዊ በሆነ የንግድ አሰራር ላይ መመስረቱን የማረጋገጥ፣

፫/ በውል የተቀበላቸውን የኢንዱስትሪ ፓርክ አገልግሎቶች ያለ አድልዎ የመስጠት፤

## SECTION FOUR
## CONDITIONS UNDER WHICH INDUSTRIAL PARK DEVELOPER, OPERATOR AND ENTERPRISE UNDERTAKE THEIR INVESTMENT ACTIVITIES

### 12.Conditions under which an Industrial Park Developer Develops a Park

Without prejudice the provisions of the Proclamation, an industrial park developer shall have the following responsibilities:

1/ provide facilities that are necessary during construction stage such as for first aid, cafeterias, toilets, and ensure the security and well-being of construction workers;

2/ carry out construction of buildings, develop infrastructure and service facilities in compliance with the requirements of these Regulations, terms of the investment permit and agreement in a timely and adequate manner;

3/ include buildings and facilities to be used for the provision of certification service regarding product quality and other requirements taking into account the investment sector on which the park focuses;

4/ transfer experience garnered regarding park development to Ethiopians;

5/ submit detailed quarterly report to the Commission regarding performance of the project particularly the performance of the industrial park land development and construction activities within the park, use of factory and other buildings.

### 13.Conditions under which an Industrial Park Operator Operates a Park

Without prejudice the provisions of the Proclamation, an industrial park operator shall have responsibility to ensure the following:

1/ activities in the park are carried out in compliance with the relevant laws and terms of the operator agreement;

2/ administration of the park is in conformity with reasonable trade practice;

3/ provision of service in the park without discrimination;

www.chilot.me

፬/ ከኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅቶች ማሕበር ጋር በመመካከር በተዘጋጀ ውስጠ ደንብ መሠረት በተለይ የሚከተሉትን ተግባራት፡-

ሀ) የግንባታ ማሻሻያዎች አግባብነት ካላቸው ሕግጋት ጋር መጣጣማቸውን የማረጋገጥ፤

ለ) በፓርኩ ውስጥ፣ በመግቢያ እና በመውጫ በሮች የሰዎችና የተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ የማሳለጥ፤

ሐ) የጭነት ማራገፊያ ተርሚናል እና የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የማድረግ፤

መ) በፓርኩ ውስጥ እና ዙሪያ ተገቢውን ፀጥታና ደህንነት የመጠበቅ፤

ሠ) የእሳትና የድንገተኛ አደጋ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሥርዓት በአግባቡ የመዘርጋት እና ዘወትር በተጠንቀቅ ላይ እንዲሆን የማድረግ፤

ረ) የፈሳሽና የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድን ጨምሮ የጋራ ቦታዎች ጽዳት የመጠበቅ፤

ሰ) የአረንጓዴ እና የጋራ ቦታዎች እንክብካቤና ልማት የማካሄድ፤

ሸ) የመሠረተ-ልማት አውታሮች በአግባቡ መጠበቃቸውን፣ መጠገናቸውንና አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸውን የማረጋገጥ፡፡

፭/ የተወሰኑ አገልግሎቶች ከሦስተኛ ወገን በውል እንዲቀርቡ የማድረግ፣

፮/ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሲያጋጥም የፀጥታና የሕግ ማስከበር አካላትን በተለይ የመንግሥት የፀጥታ ኃይል ትብብርን በመጠየቅ በፓርኩ ውስጥ ፀጥታ እና ደህንነት የማስከበር፣

፯/ በኢንዱስትሪ ፓርኩ ለተጠቃሚም ሆነ ለጉምሩክ ሕግ አፈፃፀም ምቹ የሆነና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ አሰራር የመዘርጋት፣

፰/ የኢንዱስትሪ ፓርክ አስተዳደር ዕውቀትና ክህሎት ለኢትዮጵያውያን የማስተላለፍ፣

፱/ ስለሥራ አፈጻጸሙ በተለይ ስለኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚና ድርጅት የመሬት ልማትና የግንባታ አፈጻጸም፣ የፋብሪካና ሌሎች ሕንጻዎች አጠቃቀም፣ በየሩብ ዓመቱ ዝርዝር ሪፖርት ለኮሚሽኑ የማቅርብ ኃላፊነት አለበት፡፡

**፲፬. <u>የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ሥራውን ስለሚያከናውንበት ሁኔታ</u>**

የአዋጁ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት የሚከተሉት ኃላፊነቶች አሉበት፤

፩/ የሠራተኛ የሥራ ሁኔታና ምርታማነት ትስስር ሥርዓት የመዘርጋት፤ በተለይም የጤና እንክብካቤ

4/ activities are carried out in compliance with by laws developed in consultation with the association of industrial park enterprises, in particular:

a) modifications to buildings comply with relevant laws;

b) movement of people and vehicles inside the park and at the gates is streamlined;

c) parking space and cargo terminals are properly utilised;

d) adequate security is provided inside the park and its surrounding;

e) fire and accident prevention and control system is in place and readily available for use;

f) removal of liquid and solid waste and cleanliness of common spaces is ensured;

g) develop common space and green areas and look after them;

h) properly maintain and preserve infrastructure, ensure that they are in working order;

5/ conclusion of agreement with third parties for provision of certain services;

6/ ensure security within the park, where need be, by calling upon government security forces for support;

7/ make use of modern technological means to secure the industrial park in ways that are suitable to users and implementation of customs laws;

8/ transfer to Ethiopians of knowledge and skill in regard to administration of an industrial park;

9/ submission of detailed quarterly report to the Commission regarding the discharge of its duties particularly the performance of the industrial park land development and construction activities within the park, use of factory and other buildings.

**14.<u>Conditions under which an Industrial Park Enterprise Carries on Investment</u>**

Without prejudice to the provisions of the Proclamation, an industrial park enterprise shall have the following responsibilities:

1/ put in place a system for work conditions, productivity and particularly provide access to

www.chilot.me

አገልግሎት ሽፋን፣ የሕጻናት ማቆያ፣ ካፊቴሪያዎችና እንደ አስፈላጊነቱ የመጓጓዣ አገልግሎቶች እንዲኖሩ የማድረግ፣

፪/ ዕውቀትና ክህሎት ለኢትዮጵያውያን እንዲተላለፍ የማድረግና በዚህ ረገድ ያከናወነውን ተግባር ለሚመለከታቸው መንግሥታዊ ተቋማት በየዓመቱ ሪፖርት የማቅረብ፣

፫/ በሥራ ላይ ያሰማራቸውን የአገር ውስጥ እና የውጭ አገር ሠራተኞች የተመለከተ መረጃ በየሩብ ዓመቱ ለኮሚሽኑ የመስጠት፣

፬/ የሥራ አፈጻጸሙን በተለይ የምርትና የወጪ ንግድ አፈጻጸም ሪፖርት ለኮሚሽኑ በየወሩ የማቅረብ፡፡

## ክፍል አምስት
## የአንድ ማዕከል አገልግሎትና ተያያዥ ጉዳዮች

### ፲፭. የኢንዱስትሪ ፓርክ የአንድ ማዕከል አገልግሎት

፩/ከኮሚሽኑ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የወሰደ አልሚ፣ አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት የሚከተሉትን የአንድ ማዕከል አገልግሎቶች በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ያገኛል፡-

ሀ) የኢንቨስትመንት ፈቃድ ዕድሳት፣ ማሻሻያ፣ ወይም ለውጥ ወይም ምትክ፣ ወይም ነባር የኢንቨስትመንት ሥራን ለማስፋፋት የሚሰጥ የኢንቨስትመንት ፈቃድ፣

ለ) የንግድ ምዝገባ ለውጥ ወይም ማሻሻያ ወይም ምትክ የንግድ የምስክር ወረቀት፣

ሐ) የንግድ ሥራ ፈቃድ፣ ዕድሳት ወይም ምትክ፣

መ) የንግድ ማሕበር ስም ማሻሻያ ወይም ለውጥ፣

ሠ) የንግድ ስም ምዝገባ፣ ምትክ የንግድ ስም፣ የንግድ ስም የምስክር ወረቀት ማሻሻያ ወይም ስረዛ፣

ረ) የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅቶች ማሕበር ምዝገባና እድሳት፣

ሰ) የውጭ ቀጥተኛ ካፒታል ምዝገባ፣

ሸ) ቪዛ የመስጠትና ዕድሳት፣ የመኖሪያ ፈቃድ የመስጠትና ዕድሳት፣

ቀ) የሥራ ፈቃድ መስጠት፣ ማደስ፣ መተካትና መሠረዝ፣

በ) የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ማበረታቻ እና ያለ ውጭ ምንዛሪ ፈቃድ ወደ አገር ውስጥ ዕቃ የማስገቢያ ፈቃድ፣

ተ) የገቢ ግብር ነጻ ማበረታቻ ፈቃድ፣

health care coverage, day care, cafeterias, and where appropriate, transportation;

2/ submit annual report to the relevant governmental institutions regarding activities carried out to transfer to Ethiopians knowledge and skill;

3/ submit annually to the Commission information regarding its employees, based on a format to be prepared by the Commission in consultation with pertinent governmental institutions;

4/ submit monthly report to the Commission on its performance, particularly as regards production and export.

## SECTION FIVE
## ONE-STOP SHOP SERVICE AND RELATED MATTERS

### 15. One-stop Shop Service

1/An industrial park developer, operator or enterprise that has been issued investment permit by the Commission shall have access to the following one-stop shop services at a park level:

a) renewal, amendment, change or replacement of investment permit or issuance of investment permit for expansion of investment project;

b) change or amendment of commercial registration or issuance of substitute certificate of commercial registration;

c) issuance and renewal of business license, or issuance of substitute business license;

d) amendment or change of the name of a business organisation;

e) registration of trade name, giving substitute trade name, amendment of trade name certificate or its cancellation;

f) registration and renewal of registration of the association of industrial park enterprises;

g) registration of foreign direct capital;

h) issuance and renewal of visa, issuance and renewal of residence permit;

i) issuance of work permit, its renewal, replacement and cancellation;

j) approval of exemption from customs duty and franco valuta importation of goods;

k) approval of income tax holiday;

www.chilot.me

ቸ) በአንድ የኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ከአንድ የቀረጥ ነፃ መብት ያለው ድርጅት ወደ ሌላ የቀረጥ ነፃ መብት ያለው ድርጅት የግንባታ ዕቃዎች፣ የካፒታል ዕቃዎች፣ የመለዋወጫ ዕቃዎች እና ተሽከርካሪዎች የማስተላለፍ ፈቃድ፤

ኀ) የመመስረቻ ጽሁፎች፣ የመተዳደሪያ ደንቦች ማሻሻያና ሌሎች ሰነዶች ማረጋጫ፤

ነ) ለኢንዱስትሪ ፓርክ ሠራተኞች የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር መስጠት፣ የውጭ አገር ዜግነት ያላቸው ሠራተኞች የገቢ ግብር ነፃ ማበረታቻ ውሳኔ፤

ኘ) ለኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማወራረድ፣ የቫውቸር እንዲሁም ሌሎች ከወጪ ንግድ ማበረታቻ ጋር ተያያዥ ፈቃዶችና አገልግሎቶች ፤

አ) የግብር ማሳወቅ፣ የግብር ክፍያ፣ የግብር ተመላሽ ማወራረድ፣ የግብር ኦዲት እና ከግብር ጋር ተያያዥነት ያላቸው አገልግሎቶች፤

ከ) ከአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት ጋር የተያያዙ ምዝገባዎች፤

ኸ) የስምሪት አገር ምስክር ወረቀት እና የተለየ የገበያ ዕድል ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል ደጋፊ የምስክር ወረቀቶች፣

ወ) የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ማጽደቅ እና የምስክር ወረቀት፤

ዐ) አስፈላጊ ሲሆን፣ የብቃት ማረጋገጫ እና ሌሎች በግብይት ሥርዓት የሚጠየቁ የምስክር ወረቀቶች፤

ዘ) የባንክ፣ የመድህን፣ የመርከብ ማጓጓዣ፣ የሎጂስቲክስ እና ሌሎች ከፓርኩ ጋር አግባብነት ያላቸው አገልግሎቶች፤

ዠ) የኢንዱስትሪ ፓርክ የነዋሪነት የምስክር ወረቀት፤

የ) አሠሪና ሠራተኛ መዋጮዎችን ለግል ጡረታ ፈንድ የመሰብሰብ አገልግሎት፤

ደ) ከሥራው ጋር በተያያዘ የሠራተኛውን ደኅንነትና ጤንነት የተመለከተ ክትትል እና ድጋፍ፤

ጀ) ቅሬታዎችን ማስተናገድ እና ክርክሮችን መፍታት ወይም አግባብ ባለው አካል በተለይ አማራጭ የክርክር መፍቻ መንገዶች በመጠቀም እንዲፈቱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፡፡

l) receipt and entertainment of requests for transfer of construction materials, capital goods, spare parts and motor vehicles from an industrial park enterprise entitled to exemption from customs duty to another enterprise with the same entitlement within a single industrial park;

m) authentication of documents including memorandum of association, articles of association and amendments thereto;

n) issuance of tax identification number to employees in the industrial park and communication of decisions regarding income tax holiday to expatriate employees;

o) registration of industrial park enterprises for value added tax, refund of value added tax, granting permits and rendering services such as in relation to implementation of voucher and other export incentives;

p) provision of declaration of tax, payment of tax, tax refund, tax audit and other services pertaining to tax;

q) conduct of registrations pertaining to employers and workers;

r) issuance of certificate of origin and other supporting certificates necessary to benefit from special market opportunities;

s) approval of environmental impact assessment studies and issuance of certificate;

t) issuance of a certificate of competence, and other certificates required in the marketing of products, where necessary;

u) provision of banking, insurance, shipping, logistical and other services of relevance to the park;

v) issuance of certificate of residence to industrial park residents;

w) collection of contributions from employers and employees to the private organisations pension fund;

x) follow up and give support regarding the safety and health of workers in relation to work;

y) Handling complaints and resolving disputes or creating conducive condition for resolution of disputes by appropriate organs, especially using alternative dispute resolution methods.

www.chilot.me

፪/ ሁሉም አግባብነት ያላቸው የመንግሥት ተቋማት ለኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚዎች መስጠት የሚገባቸውን አገልግሎቶች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርክ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ቅርንጫፍ ገብተው የመስጠት ወይም ኮሚሽኑን ወይም ሌሎች አግባብነት ያላቸው ተቋማትን በመወከል አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡

፫/ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ወይም አስተዳዳሪ በፓርኩ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ውስጥ በመታቀፍ የውሃ፣ የኤሌክትሪክ፣ የቴሌኮም (የድምጽ፣ የዳታ፣ የቪዲዮና ተዛማጅ አገልግሎቶች)፣ የፈሳሽ እና የደረቅ ቆሻሻ የማስወገድ እና ሌሎች አስፈላጊ አገልግሎቶችን በቀጥታ ራሱ ወይም በሌላ አቅራቢ እንዲሰጡ ያደርጋል፡፡

፬/ የአንድ ማዕከል አገልግሎት የመስጠት ኃላፊነት ያለበት መንግሥታዊ ተቋም የኢንዱስትሪ ፓርክን ባሕሪይ ከግምት ውስጥ ያስገባ ልዩ መዋቅርና ዝርዝር የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት አለበት፡፡

፭/ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን የተቀናጀና ውጤታማ ለማድረግ የመንግስት አስፈጻሚ አካላት በኮሚሽኑ አስተባባሪነት ስምምነት መፈራረም አለባቸው፡፡

**፲፮. <u>የቪዛ እና የመኖሪያ ፈቃድ አገልግሎት ስለመስጠት</u>**

፩/ ኮሚሽኑ ከኢንቨስትመንት ጋር በተያያዘ ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡ የውጭ አገር ዜጎች እና በእነርሱ ሥር ለሚተዳደሩ ቤተሰቦቻቸው ተገቢውን ቪዛ እና የመኖሪያ ፈቃድ እንዲያገኙ ሊጠይቅላቸው ይችላል፡፡

፪/ ከኢንቨስትመንት ጋር በተያያዘ የውጭ አገር ዜጋ ከሦስተኛ አገር ሆኖ የቪዛ ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ ወደ መኖሪያ አገሩ መመለስ ሳያስፈልገው ካለበት አገር የቪዛ ጥያቄ ሊያቀርብና ሊሰጠው ይችላል፡፡

፫/ ለኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ወይም ድርጅት ባለቤት ወይም ባለአክስዮን የ፭(አምስት) ዓመት የብዙ ጊዜ መመላለሻ ቪዛ ወይም የመኖሪያ ፈቃድ በኮሚሽኑ በሚቀርብ ማረጋገጫ መነሻነት ሊሰጥ ይችላል፡፡

፬/ በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የሚሰራ የውጭ አገር ዜግነት ያለው አስተዳዳሪ፣ የኢንዱስትሪ ፓርክ ምርት ገዢ፣ ሠራተኛ፣ የሥራ ኃላፊ፣ የዋና መስሪያ ቤት ሥራ አስፈጻሚ፣ የቦርድ አባል ወይም ከፍተኛ ባለሙያ በኮሚሽኑ በሚቀርብ ማረጋገጫ መነሻነት የ፫ (ሦስት) ዓመት የብዙ ጊዜ መመላለሻ ቪዛ ወይም የመኖሪያ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2/ All relevant government organs that are required to give service to industrial park end-users shall have duty to provide service either presence in the one-stop shop service or designate the Commission or another appropriate institution to provide such service on their behalf within a park.

3/ An industrial park developer or operator shall, as part of one-stop-shop service within each park, provide water, electricity, telecom including voice, video, data and other related services, remove liquid and solid waste and other necessary services either directly or through the instrumentality of a third person.

4/ Governmental institutions that are responsible for rendering one-stop shop service in the park shall set up structure and detailed operational procedures that take into account the nature of industrial parks.

5/ Relevant government organs shall, under the coordination of the Commission, conclude agreement among themselves with the view integrating and making one-stop shop service effective.

**16. <u>Visa and Residence Permit</u>**

1/ The Commission may facilitate the processing of visa and residence permit applications of foreign citizens who come to Ethiopia in relation to investment and that of their dependent family members.

2/ A foreign citizen who happens to be outside his country of residence may apply for Ethiopian visa from the third country where the reason for travel to Ethiopia pertains to investment.

3/ A multiple entry visa, that is valid for 5 (five) years or residence permit may be issued, based on an assurance from the Commission, to an owner or shareholder of an industrial park developer or enterprise.

4/ A multiple entry visa, that is valid for 3 (three) years or residence permit may be issued, based on an assurance from the Commission, to a foreign operator that works in an industrial park, to an industrial park product buyer, worker, manager, executive officer from head quarters, board member or high level professional staff.

www.chilot.me

**፲፯.የሥራ ፈቃድ ስለመስጠት**

፩/ ኮሚሽኑ ከኢንዱስትሪ ፓርክ ጋር በተያያዘ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለሰጠው አልሚ፣ አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት ለሚቀጥረው የውጭ አገር ዜጋ የሥራ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

፪/ ከኢንዱስትሪ ፓርክ ጋር በተያያዘ በውጭ አገር ሠራተኛነት ተቀጥሮ ወደ ኢትዮጵያ የገባ ሠራተኛ የትዳር አጋር በአገሪቱ ውስጥ አብሮ የሚኖር ከሆነ የሥራ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፡፡

**፲፰. ስለዕውቀት፣ ክህሎትና ቴክኖሎጂ ሽግግር**

፩/ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው አካላት ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ጋር በተያያዘ የሠራተኞች ምልመላ፣ የክህሎት ልማትና ሽግግር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርና ማሳደግ እንዲሁም የግብዓት አቅርቦትና የገበያ ትስስር ተግባራዊ እንዲሆን ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡

፪/ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የክህሎትና እውቀት ሽግግር ወደ ኢትዮጵያውያን ሠራተኞች እንዲደረግ የሚያስችል የስልጠና መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፣ ስልጠናውም በኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ፣ አስተዳዳሪና ድርጅት እንዲሰጥ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፡፡

፫/ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የቴክኖሎጂ ሽግግሩ እንዲፋጠን የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያስፈጽማል፣ በተለይ በመንግሥትና በኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅቶች አጋርነት የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ቴክኖሎጂ ማሳደግ፣ የኢንዱስትሪ ምርታማነትና የምርት ጥራት የማሳደግ እንዲሁም ጥናትና ምርምር እንዲካሄድ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

፬/ በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት ኢንስቲትዩቶች እንደአስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ እንዲከፍቱ ያደርጋል ወይም ባለሙያዎች ይመድባል፡፡

## ክፍል ስድስት
## የኢንዱስትሪ ፓርክን የተመለከተ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት

**፲፱. የጉምሩክ ቁጥጥር**

፩/ ማንኛውም የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ይከናወናል፡፡

፪/ የኢንዱስትሪ ፓርክ ሙሉ በሙሉ ወይም ከፊል የኢንዱስትሪ ፓርክ የጉምሩክ ቁጥጥር ክልል ይኖረዋል፡፡

**17. Issuance of Work Permit**

1/ A work permit shall be issued by the Commission to a foreign citizen to be employed by an industrial park developer, operator or enterprises that has been given investment permit in relation to an industrial park.

2/ A work permit may be issued to the spouse of a foreign industrial park worker who lives in Ethiopia.

**18. Transfer of Knowledge, Skills and Technology**

1/ The Ministry of Industry and other relevant organs shall make sure that industrial parks recruit workers, foster skills development and transfer, and transfer and upgrading of technology; they shall also ensure supply of input and creation of market linkage; and render support in regard to the realization of these.

2/ The Ministry of Industry shall design training programs that enable transfer of skills and knowledge to Ethiopian workers; and support and follow up to see it that an industrial park developer, operator and enterprise provide the training.

3/ The Ministry of Industry shall, in collaboration with relevant bodies, put in place mechanisms that facilitate technology transfer; particularly, the Ministry shall have the responsibility to foster partnership between government and industrial park enterprises with the view to enhancing the transfer and advancement of technology, increase productivity and quality of industrial products and cause the conduct of studies and research.

4/ The Ministry of Industry shall cause institutes accountable to open its branch offices, as may be appropriate, within parks or assign experts in order to discharge its responsibilities under the Proclamation and these Regulations.

## SECTION SIX
## CUSTOMS PROCEDURE AS CONCERNS INDUSTRIAL PARK

**19. Customs Control**

1/ All customs procedures shall be completed in an industrial park.

2/ An industrial park may either in its entirety or partly be a customs controlled area.

www.chilot.me

፫/ ከኢንዱስትሪ ፓርክ ጋር በተያያዘ የጉምሩክ ቁጥጥር የሚካሄደው በጉምሩክ ክልል መግቢያና መውጫ በሮች እንዲሁም በኢንዱስትሪ ፓርኮች በሮች ላይ ይሆናል፡፡

፬/ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ወይም አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት ወደ ኢንዱስትሪ ፓርክ የጉምሩክ ቁጥጥር ክልል የተለያዩ ዕቃዎች ሲያስገባና ሲያስወጣ በተቃለለ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ይስተናገዳል፡፡

፭/ ማንኛውም የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ከጉምሩክ ክልል መግቢያ በር ወደ ኢንዱስትሪ ፓርክ የሚያስተላልፈው ጭነት እስከ ኢንዱስትሪ ፓርክ ድረስ በሚጓጓዝበት ወቅት አይቆምም፣ አይፈተሽም፣ ነገር ግን ዕቃው በኮንቴነር የታሸገ እና የዕቃው ማጓጓዣ ሰነድም መድረሻ ጣቢያ የሆነው የኢንዱስትሪ ፓርክ ስም መገለጽ አለበት፡፡

፮/ በኢንዱስትሪ ፓርክ የሚገኝ ምርቱን ሙሉ ለሙሉ ወደ ውጭ አገር የሚልክ የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት የምርት ግብዓቶችን ከውጭ አገር ወደ ኢንዱስትሪ ፓርክ ሲያስገባ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ አይከፍልም፣ ሆኖም ድርጅቱ ምርቱን በከፊል አገር ውስጥ የሚሸጥ ከሆነ በልዩነቱ ተገቢውን ቀረጥና ታክስ ይከፍላል ፡፡

፯/ ማንኛውም የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ምርቱን በኢንዱስትሪ ፓርኩ ወይም በሌላ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ለሚገኝና ምርቱን ወደ ውጪ ለሚልክ ድርጅት በግብዓትነት ሲያቀርብ ያለቀረጥና ታክስ መሸጥ ይችላል፡፡

፰/ በጉምሩክ ክልል ውስጥ ያለ ድርጅት በአገር ውስጥ የተመረተ ግብዓትን ምርቱን ወደ ውጭ አገር ለሚልክ የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ሲያቀርብ ያለ ቀረጥና ታክስ መሸጥ ይችላል፣ ይህ የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅትም ከጉምሩክ ክልል የገዛውን የምርት ግብዓት ተጠቅሞ የሚያመርተው ምርት ወደ ውጭ አገር የሚልክ ከሆነ በዚህ የምርት ግብዓት ላይ ታክስና ቀረጥ አይጠየቅም፡፡

፱/ ምርቱን ሙሉ በሙሉ ወደ ውጭ አገር ለመላክ የተስማማ የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ከውጭ አገር ያለቀረጥና ታክስ ያስገባውን ጥሬ ዕቃ እስከ አንድ ዓመት ማቆየት ይችላል፣ ሆኖም ድርጅቱ ጥሬ ዕቃውን ከአንድ ዓመት በላይ ለማቆየት አሳማኝ ምክንያት ካቀረበ ኮሚሽኑ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፲/ ሙሉ ምርቱን ወደ ውጭ አገር ለመላክ የተስማማ የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት በማናቸውም ሁኔታ በጉምሩክ ክልል ውስጥ መሸጥ አይፈቀድለትም፣ ሆኖም በልዩ ሁኔታ በቦርዱ የተፈቀደለት ከሆነ ተገቢውን የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ከፍሎ በጉምሩክ ክልል መሸጥ ይችላል፡፡

3/ Customs control in connection with industrial parks shall be carried out at the entry and exit gates of the customs territory as well as at the gates of the industrial parks.

4/ Goods transported by an industrial park developer or operator or enterprise to or from customs controlled area of an industrial park shall be cleared by simplified customs procedure.

5/ Cargo shipped by an industrial park enterprise from port of entry into the customs territory to an industrial park shall neither be stopped nor examined en route. The goods shall, however, be sealed in a container and the shipping documents that clearly indicate the industrial park to which the cargo is destined.

6/ An industrial park enterprise that has undertaken to export its entire produce shall be exempted from any customs duty and tax on raw materials it may import; provided, however, where an industrial park enterprise sells parts of its produce to the customs territory, it shall be subject to appropriate customs duty and tax on the difference.

7/ An industrial park enterprise that sells its products as input to another industrial park enterprise that exports its produce shall not be subject to payment of customs duty and tax.

8/ Any enterprise located within the customs territory that supplies input produced anywhere within the country to an industrial park enterprise engaged in export shall not be subject to payment of any customs duty or tax on such transaction; an industrial park enterprise that exports products that it produced using input that it purchased in the customs territory shall also not be subject to payment of customs duty and tax on the input used.

9/ An industrial park enterprise that has undertaken to export its entire produce may keep up to one year raw material that it imported without payment of customs duty and tax. Where such enterprise establishes good cause to retain such raw material for a period exceeding one year, the Commission may allow additional time..

10/ An industrial park enterprise that has undertaken to export its entire produce may not, under any circumstance, sell its products within the customs territory; provided, however, it may under special circumstances, if authorised by the Board, sell its products within the customs territory subject to

www.chilot.me

፲፩/ ሙሉ ምርቱን ወደ ውጭ አገር እንዲልክ የሚጠበቅበት የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ያመረተው ምርት የኤክስፖርት ደረጃውን ያልጠበቀ ወይም ምርቱ ወደ ውጭ ከተላከ በኋላ ጉድለት ኖሮት የተመለሰ ስለመሆኑ ማስረጃ ካቀረበ፡-

ሀ) በኮሚሽኑ ሲፈቀድ በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ በተዘጋጀ ልዩ ቦታ በዓመት ሁለት ጊዜ ብቻ ከአንድ ሳምንት ለማይበልጥ ተከታታይ ቀናት ልዩ የሽያጭ መርሀ-ግብር ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፍሎበት ሊሸጠው ወይም፣

ለ) በአገሪቱ ውስጥ በሕግ አግባብ ለተቋቋመ የበጎ አድራጎት ድርጅት በስጦታ ሊሰጠው ወይም፣

ሐ) በሌላ መንገድ ሊያስወግደው ይችላል፡፡

፲፪/ የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ተረፈ ምርቱን የተጨማሪ እሴት ታክስ ብቻ ከፍሎ በጉምሩክ ክልል ውስጥ መሸጥ ይችላል፤ ድርጅቱ የተጨማሪ እሴት ታክሱን የሚከፍለው ግብይቱ በሚከናወንበት ጊዜ በሚኖረው ዋጋ ላይ ይሆናል፡፡

፲፫/ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ወይም ድርጅት ከውጭ ያስመጣቸውን የተበላሹ ወይም እክል ያለባቸውን የካፒታል ዕቃዎች፣ መለዋወጫዎች እና አክሰሰሪዎች ለባለሥልጣኑ የዋስትና ደብዳቤ በማቅረብ ወደ ውጭ ልኮ መተካት ወይም ማስጠገን ይችላል፤ ይህንን በተመለከተ ከባለሥልጣኑ ምንም ክፍያ አይጠየቅም፡፡

፲፬/ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ወይም ድርጅት የውጭ ምንዛሪ ፈቃድ ሳይጠይቅ ወደ አገር ውስጥ ያስገባውን ዕቃ ቀረጥና ታክስ የማይፈለግበት ከሆነ ከአገር መልሶ የሚወጣ ዕቃ ላይ የተጣለ ክፍያ ሳይፈጽም ባለሥልጣኑን በማስፈቀድ ማስወጣት ይችላል፡፡

፲፭/የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈበት ወይም ጉዳት የደረሰበት የምርት ግብዓት ከሚመለከተው የመንግሥት ተቋም ማረጋገጫ ለባለሥልጣኑ በማቅረብ እንዲወገድ ማድረግ ይችላል፡፡

፳. <u>በጉምሩክ አሰራር ላይ የሚፈጸም ጥሰት</u>

የጉምሩክንና ሌሎች ሕግጋትን የጣሰ የኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

payment of appropriate customs duty and tax.

11/ Where an industrial park enterprise that is required to export its entire produce provides proof that its products could not meet export standards or its produce has been sent back after being exported owing to defects:

a) may, after securing permission from the Commission, sell such products at a special sales event to be organised only twice per year each for a continuous period not exceeding one week within the park at a place designated for such purpose, subject to payment of value added tax or;

b) may donate such products to a charity lawfully established within the country or;

c) get rid of such products by other means.

12/ An industrial park enterprise may sell by-products within the customs territory subject to the payment of only value added tax. The value added tax due from the enterprise shall be computed on the basis of the price at which the enterprise sells the by-products.

13/ An industrial park developer or enterprise may, by furnishing a letter of guarantee to the Authority, send abroad defective, damaged or incomplete capital goods, spare parts and accessories and have them replaced or repaired; and the Authority may not require any payment as regards this.

14/ Where customs duty or tax is not due on goods imported franco valuta by an industrial park developer or enterprise such goods may be sent abroad by the industrial park developer or enterprise, by securing permission from the Authority, without making payments that are charged in relation to goods sent back abroad.

15/ An industrial park enterprise may, by adducing evidence to the Authority from a relevant governmental institution, cause the removal of input that has expired or is defective.

**20. <u>Violation of Customs Procedures</u>**

An industrial park end-user that violates the customs and other laws shall be held accountable under the relevant law.

www.chilot.me

## ክፍል ሰባት
## ቅሬታ እና ክርክር ስለሚፈታበት ሥርዓት

**፳፩. መርሆዎች**

፩/ በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የሚነሳ የአስተዳደር ቅሬታ፣ የፍትሐብሔር እና የንግድ ክርክር ቀልጣፋ፣ ሚዛናዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ ይፈታል፡፡

፪/ በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ በአሠሪና ሠራተኛ መካከል የሚፈጠር ቅሬታና የወል ወይም የተናጠል የሥራ ክርክር ለአማራጭ የክርክር መፍቻ ዘዴዎች ቅድሚያ በመስጠት በሠራተኛና አሠሪ ሕግ መሠረት ይፈታል፡፡

**፳፪.አስተዳደራዊ እርምጃ**

፩/ ፈቃዱን ለማግኘት የተቀመጡትን ቅድመ-ሁኔታዎች፣ ይህን ደንብ፣ መመሪያዎችን ወይም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሕግጋት የጣሰው የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ወይም አስተዳዳሪ ከሆነ ቦርዱ፣ የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት ከሆነ ደግሞ ኮሚሽኑ ከስልሳ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡

፪/ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው አልሚ፣ አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተሰጠው ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ ካልወሰደ እንደአግባብነቱ በቦርዱ ወይም በኮሚሽኑ ከስልሳ ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ፈቃዱ ሊታገድ ይችላል፡፡

፫/ ፈቃዱ የታገደበት የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ ወይም አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተሰጠው ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን ማስተካከያ አድርጎ ወደ ሥራ ካልተመለሰ ቦርዱ የሦስተኛ ወገኖችን መብት ለማስጠበቅ ሲል አግባብ ባለው አካል ጊዜያዊ ባለአደራ እንዲሰየምና ቀጣይ እርምጃ እንዲወሰድ ሊወስን ይችላል፡፡

**፳፫.በኮሚሽኑ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ስለማቅረብ**

፩/ ማንኛውም የኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚ በኮሚሽኑ በሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ ላይ ለቦርዱ ቅሬታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፪/ በኮሚሽኑ በተሰጠ ውሳኔ ወይም በተወሰደ አስተዳደራዊ እርምጃ ላይ ቅር በመሰኘት ለቦርዱ የሚቀርብ ማንኛውም ቅሬታ በኮሚሽኑ ከተሰጠው ውሳኔ ወይም ከተወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃ ግልባጭ ጋር በጽሁፍ መቅረብ አለበት፡፡

፫/ ኮሚሽኑ የሰጠው ውሳኔ እና የወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃ የሚመለከተው ወገን በጽሑፍ እንዲሰጠው ከጠየቀ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ ሊሰጠው ይገባል፡፡

## SECTION SEVEN
## COMPLAINT HANDLING AND DISPUTE RESOLUTION

**21. Principles**

1/ Administrative complaints, civil and commercial disputes that arise in an industrial park shall be settled in efficient, effective and balanced manner.

2/ Complaints and collective or individual labour disputes that arise between a worker and his employer in an industrial park shall be resolved pursuant to the Labour Law by giving priority to alternative dispute mechanism.

**22.Administrative Measure**

1/ Where an industrial park developer or operator violates the conditions for the issuance of its permit, these Regulations, directives or other relevant laws, the Board shall issue it a warning requiring that corrective measures be taken in less than sixty days; a similar warning shall be issued by the Commission where the foregoing violation is committed by an industrial park enterprise.

2/ Where an industrial park developer, operator or enterprise fails to take corrective measures within the time limit provided for under sub-article (1) of this Article, the Board, or as may be appropriate the Commission, may suspend its permit for not more than sixty days.

3/ Where an industrial park developer or operator or enterprise whose permit has been suspended fails to take corrective measures and fails to resume work within the time limit fixed pursuant to sub-article (2) of this Article, the Board may decide that the matter be referred to an appropriate body for a provisional trustee that takes appropriate measures to preserve the rights of third parties be appointed.

**23. Lodging Complaint against Decision of the Commission**

1/ Any industrial park end-user may lodge complaint to the Board against administrative measures taken by the Commission.

2/ The complaint against the decision or administrative measure taken by the Commission shall be made in writing; a copy of the decision or measure taken by the Commission shall be submitted together with the pleading.

3/ Where a party with vested interest requests that the decision or administrative measure taken by the Commission be given to it in writing, the Commission shall give that within seven official working days of the request.

www.chilot.me

**፳፬.<u>በቦርዱ ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ ይግባኝ</u>**

፩/ በቦርዱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ጉዳዩን አግባብ ላለው ፍርድ ቤት በይግባኝ መውሰድ ይችላል፡፡

፪/ ቅሬታ አቅራቢው የቦርዱ ውሳኔ ግልባጭ በጽሑፍ እንዲሰጠው ከጠየቀ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ በቦርዱ ጽሕፈት ቤት ሊሰጠው ይገባል፡፡

**፳፭.<u>በሌሎች መንግሥታዊ አካላት ላይ ስለሚቀርብ ቅሬታ</u>**

፩/ የኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚ በሌሎች ማናቸውም መንግሥታዊ አካላት ከኢንዱስትሪ ፓርክ ጋር በተያያዘ በሚሰጥ ውሳኔ ወይም በሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ ላይ ቅሬታውን ለኮሚሽኑ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፪/ ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የቀረበን ቅሬታ በየኢንዱስትሪ ፓርኩ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ውስጥ መፍትሔ እንዲያገኝ ማድረግ ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተጠቀሰው ቅሬታ ለኮሚሽኑ የኢንዱስትሪ ፓርክ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ቀርቦ ከታየ በኋላ ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው ባለጉዳዮች ጋር በመነጋገር በሰላሳ ቀናት ውስጥ የመፍትሄ ሀሳብ በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፡፡

**፳፮. <u>ቅሬታን በእርቅ ስለመፍታት</u>**

፩/ በኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚዎች መካከል የሚነሱ ቅሬታዎችን ኮሚሽኑ በአንድ ማዕከል አገልግሎት በእርቅ መፍትሔ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አገልግሎት የሚሰጠው ቅሬታ ውስጥ የገቡት ወገኖች የአስታራቂነት ጥያቄያቸውን ተስማምተው በጽሑፍ ለአንድ ማዕከል አገልግሎት ሲያቀርቡ ብቻ ነው፡፡

፫/ የአስታራቂነት ጥያቄ ለኮሚሽኑ በቀረበ ጊዜ የአንድ ማዕከል አገልግሎት የቅሬታ አፈታት ባለሙያ እንደአስፈላጊነቱ ከባለጉዳዮቹ ጋር በመነጋገር እጅግ ቢዘገይ ቅሬታው በቀረበ ሰላሳ ቀናት ውስጥ የመጨረሻ የመፍትሔ ሐሳብ በጽሁፍ ያቀርባል፡፡

፬/ በኮሚሽኑ የቀረበውን የመፍትሔ ሀሳብ እንደሚቀበሉት ቅሬታ ውስጥ የገቡት ወገኖች በጽሁፍ ያረጋገጡ እንደሆነ የቀረበው ሀሳብ አስገዳጅነት ይኖረዋል፡፡

፭/ የእርቅ ሀሳቡ ይፋ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ሁሉም ወገኖች የእርቅ ሀሳቡን እንደተቀበሉ በጽሑፍ ካላረጋገጡ እንዳልተቀበሉት ይቆጠራል፡፡

**24. <u>Appeal Against Decision of the Board</u>**

1/ A party aggrieved by a decision of the Board may lodge appeal to an appropriate court.

2/ Where a complainant requests the copy of decision of the Board be given to him in writing, the Secretariat of the Board shall give it within seven official working days of the request.

**25. <u>Complaints Lodged Against Other Government Institutions</u>**

1/ An industrial park end-user may submit complaint to the Commission against decisions made and administrative measures taken by any other government institution in relation to an industrial park.

2/ The Commission may cause resolution of complaint submitted pursuant to sub-article (1) of this Article at each industrial park's one-stop shop service.

3/ Where a complaint is submitted to the one-stop shop service for resolution pursuant to sub-article (1) of this Article, the Commission shall consult the relevant parties and come up with a written recommendation to solve the grievance, within thirty days of the submission.

**26. <u>Conciliation</u>**

1/ The Commission shall cause resolution of disputes arising between industrial park end-users through negotiation at the one-stop shop service.

2/ The service specified under sub-article (1) of this Article shall be provided only if the parties to the dispute agree to seek that and submit their request in writing.

3/ Where a request for conciliation service is submitted to the Commission, the conciliator at the one-stop shop service shall consult the relevant parties, if need be, and come up with a written final recommendation to solve the dispute, within thirty days of submission of the complaint.

4/ The parties shall be bound by the terms of the recommendation drawn up by the Commission only if they in writing confirm their acceptance.

5/ The recommendations shall be deemed rejected, if all the parties to the dispute fail to in writing confirm their acceptance of the terms of recommendation within fifteen days from the time such recommendations were made known to them.

www.chilot.me

፮/ በእርቅ ሂደት የሚኖር ወጪ ተገልጋዮቹ ይሸፍናሉ፤ ይህንንም አስቀድመው ሊስማሙ ይገባል፡፡

**፳፯.በግልግል ዳኛ ስለመጨረስ**

፩/የኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚዎች ቅሬታቸውን በግልግል ዳኛ ለመጨረስ መስማማት ይችላሉ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ስምምነት በጽሑፍ መደረግ አለበት፤ ዝርዝሩ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር ፫ሺ፫፻፳፭ እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት ይወሰናል፡፡

**፳፰.የግልግል ዳኛ መሆን የሚችሉ ባለሙያዎች ዝርዝር**

፩/ ኮሚሽኑ ከኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚዎች የሚቀርበውን ጥቆማ መሠረት በማድረግ በግልግል ዳኝነት ለመስራት ተአማኒነትና የሙያ ብቃት ያላቸው ሰዎች ስም ዝርዝር ያዘጋጃል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን ዝርዝር ኮሚሽኑ በየሁለት ዓመቱ ወቅታዊ ያደርጋል፡፡

**፳፱. የግልግል ዳኛ አመራረጥ**

፩/ክርክራቸውን በግልግል ዳኛ ለመጨረስ የተሰማ ሙ ወገኖች በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፰ ከተመለከተው ዝርዝር ውስጥ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው በግልግል ዳኝነት መምረጥ ይችላሉ፡፡

፪/ የግልግል ዳኞች ስንት እንደሚሆኑ ወይም እንዴት እንደሚመረጡ ስምምነቱ ያላመላከተ እንደሆነ እያንዳንዱ ወገን አንድ የግልግለ ዳኛ ይመርጣል፡፡

፫/ ተቃራኒ የውል ቃል ከሌለ በቀር የግልግል ዳኞች ብዛት በጥንድ የሚ ቆጠሩ እንደሆነ ዳኞቹ ወደ ሥራው ከመግባታቸው በፊት አንድ ሌላ የግልግል ዳኛ ይመርጣሉ፡፡ ይኸውም የተመረጠው የግልግል ዳኛ ለግልግል ዳኝነቱ ሰብሳቢ ይሆናል፡፡ በግልግል ዳኞቹ መካከል ስምምነት የሌለ እንደሆነ ከተዋዋይ ወገኖች አንዱ በሚያቀርበው ጥያቄ የአዲስ አበባ የንግድና ዘርፍ ማህበር የግልግል ኢንስቲትዩት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፰ ከተመለከተው ዝርዝር ውስጥ ይመርጣል፡፡

፬/ ብዛታቸው በጥንድ የማይቆጠሩ እንደሆነ የግልግል ዳኞቹ ከመካከላቸው ሰብሳቢ የሚሆነውን ይመርጣሉ፡፡ በግልግል ዳኞቹ መካከል ስምምነት የሌለ እንደሆነ ከተዋዋይ ወገኖች አንዱ በሚያቀርበው ጥያቄ የአዲስ አበባ የንግድና ዘርፍ ማህበር የግልግል ኢንስቲትዩት ከግልግል ዳኞቹ መካከል ለግልግል ዳኝነቱ ሰብሳቢ ይሾማል፡፡

6/ The parties shall settle expenses incurred in connection with the conciliation; and they shall undertake to do that beforehand.

**27. Resolution by Arbitration**

1/ Industrial park end-users may agree to resolve disputes between themselves by arbitration.

2/ The agreement referred to under sub-article (1) of this Article shall be concluded in writing; the details shall be governed by Article 3325 and the subsequent provisions of the Civil Code of Ethiopia.

**28. Roster of Professionals that may Serve as Arbitrators**

1/ The Commission shall, based on the recommendation of industrial park end-users, compile a roster of credible professionals that can serve as arbitrators.

2/ The Commission shall update the roster specified under sub-article (1) of this Article biennially.

**29. Appointment of Arbitrator**

1/ Parties that have agreed to resolve their differences by arbitration may appoint as an arbitrator a person that appears on the roster specified under Article 28 of these Regulation or any other person.

2/ Where the arbitration agreement fails to specify the number of arbitrators or the manner in which they shall be appointed, each party shall appoint one arbitrator.

3/ Unless otherwise agreed, where there is an even number of arbitrators, they shall, before assuming their functions, appoint another arbitrator who shall as of right preside over the arbitration tribunal. Where the arbitrators fail to reach agreement, the Arbitration Institute of Addis Ababa Chamber of Commerce and Sectoral Association shall, upon the request of one of the parties to the dispute, appoint an arbitrator from the roster specified under Article 28 of these Regulations.

4/ Where their number is odd, the arbitrators shall appoint the presiding arbitrator from among themselves. Where the arbitrators fail to reach agreement, the Arbitration Institute of Addis Ababa Chamber of Commerce and Sectoral Association shall, upon the request of one of the parties to the dispute, appoint the presiding arbitrator from among the arbitrators.

www.chilot.me

**፴. ተፈጻሚነት የሚኖረው ሕግ**

ቅሬታቸውን በግልግል ዳኝነት ለመጨረስ የተስማሙ የኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚዎች ጉዳያቸው የሚፈታበትን መሠረታዊና የሥነ-ሥርዓት ሕግ መምረጥ ይችላሉ፡፡

**፴፩. የግልግል ዳኛ የአገልግሎት አበል**

ኮሚሽኑ አግባብ ካለው አካል ጋር በመመካከር በኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚዎች መካከል በሚደረግ የግልግል ዳኝነት የግልግል ዳኛ ሆነው የሚያገለግሉ ሰዎች የሚከፈላቸውን አበል ለመወሰን የሚረዳ የክፍያ ተመን ሰንጠረዥ ያዘጋጃል፤ የተመን ሰንጠረዡም በየሁለት ዓመቱ ወቅታዊ ያደረጋል፡፡

**፴፪.ተዘዋዋሪ ችሎት በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ስለሚያስችልበት ሁኔታ**

ኮሚሽኑ ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጋር በመመካከር አግባብነት ያለው የፌደራል ፍርድ ቤት ተዘዋዋሪ ችሎት በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚያስችልበት ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

**ክፍል ስምንት**
**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

**፴፫.የግል መገልገያ ዕቃዎች**

፩/ በኢንዱስትሪ ፓርክ የተሰማራ የውጭ ባለሀብት ወይም ከውጭ አገር የተመለሰ ኢትዮጵያዊ ወይም የውጭ አገር ዜግነት ያለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ በሚሰራበት ጊዜ የግል መገልገያ ዕቃዎች እንደ የሳሎን/የመኝታ ቤት፣ የወጥ ቤት፣ የባኞ ቤት እና የስፖርት ዕቃዎች፣ ላፕ ቶፕ እና ዴስክ ቶፕ ኮምፒውተሮች፣ የሙዚቃ መሳሪያ፣ ካሜራ፣ ኤሌክትሮኒክስ፣ ቲቪ፣ ሲዲ ማጫወቻ እና የመሳሰሉ ሌሎች ልዩ ልዩ ዕቃዎች ያለቀረጥና ታክስ ከውጭ አገር ማስገባት ይችላል፤ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፪/ በኢንዱስትሪ ፓርክ የተሰማራ የውጭ ባለሀብት ወይም ከውጭ አገር የተመለሰ ኢትዮጵያዊ ወይም የውጭ አገር ዜግነት ያለው ትውልደ ኢትዮጵያዊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ወደ አገር ውስጥ ያስገባቸው የግል መገልገያ ዕቃዎች፡-

ሀ) ተመሳሳይ መብት ላለው ሰው ያለቀረጥና ታክስ ማስተላለፍ ይችላል፤

ለ) አስቀድሞ ተገቢውን ቀረጥና ታክስ በመክፈል ለራሱ ከፓርክ ውጪ ሊወስደው ወይም ተመሳሳይ መብት ለሌለው ሰው ማስተላለፍ ይችላል፡፡

**30.Applicable Law**

Industrial park end-users that have agreed to resolve their differences by arbitration are at liberty to choose the substantive and procedural law to be applied by the tribunal.

**31.Arbitrator Fee**

The Commission shall, in consultation with appropriate bodies, prepare arbitration rate of fee schedule to be applied to determine fees due to arbitrators that resolve disputes among industrial park end-users.

**32.Assignment of Federal Court Circuit Bench**

The Commission shall, in consultation with the Federal Supreme Court, facilitate conditions for the assignment of a circuit bench of appropriate federal court in industrial parks.

**SECTION EIGHT**
**MISCELLANEOUS PROVISIONS**

**33.Personal Effects**

1/ A foreign investor engaged in an industrial park or an Ethiopian that resides abroad or a person of Ethiopian origin may import duty-free and without paying other taxes personal effects such as those used in living room, bedroom, kitchen, bathroom, sports appliances, lap top and desk top computers, musical instruments, camera, electronic gadgets, TV, CD player, for use if he lives or works in an industrial park; the details of which shall be prescribed by a directive.

2/ A foreign investor engaged in an industrial park or an Ethiopian that resides abroad or a person of Ethiopian origin that has imported personal effects pursuant to sub-article (1) of this Article may:

a) transfer such goods to another person with similar rights without payment of customs duty and tax;

b) Transfer such goods to another person that does not have similar rights or take them outside the park for his own use subject to the payment of appropriate customs duty and tax in advance.

www.chilot.me

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት መብቱን ማስተላለፍ የሚፈልግ ሰው ከማስተላለፉ በፊት ኮሚሽኑን ማስፈቀድ አለበት።

**፴፬.ከደመወዝ ገቢ ግብር ነፃ ስለመሆን**

ምርቱን ወደ ውጭ አገር ለመላክ የተስማማ የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት የንግድ ሥራ ፈቃድ ካወጣበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት የመጀመሪያ አምስት ተከታታይ ዓመታት ውስጥ የሚቀጥራቸው ባለሙያ የውጭ አገር ዜጎች ከደመወዝ ገቢ ግብር ነፃ ይሆናሉ፡፡

**፴፭.የሦስትዮሽ አሰራር ኮሚቴ**

፩/ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ እንደሁኔታው የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ፣ አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት አሰሪዎች እና የሠራተኛ ተወካይ የሚገኙበት የሦስትዮሽ አሰራር ኮሚቴ ይቋቋማል።

፪/ የሦስትዮሽ አሰራር ኮሚቴው፡-

ሀ) ቀጣይነት ያለው ምክክር በማድረግ የሠራተኛ መብትና ግዴታ መከበሩን ማረጋገጥ፣ ግጭት እንዳይከሰት አመቺ ሁኔታ የመፍጠር፣

ለ) ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር በመመካከር የእውቀት፣ ክህሎትና ቴክኖሎጂ ሽግግር መደረጉን በማረጋገጥ ምርታማነት እንዲጨምር የማድረግ፣

ሐ) ሌሎች የኢንዱስትሪ ሰላም ለማስፈን የሚረዱ ተግባራትን የማከናወን ኃላፊነት አለበት፡፡

፫/ ኮሚሽኑም ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር በመመካከር ኮሚቴው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ተግባሩን በአግባቡ ስለማከናወኑ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤ይቆጣጠራል፡፡

**፴፮. ሕግ ስለማስከበርና የመረጃ ልውውጥ**

፩/ ኮሚሽኑ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ አግባብነት ያላቸው የፀጥታና የሕግ አስከባሪ አካላት ከኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ፣ አስተዳዳሪ ወይም ድርጅት ጋር በትብብርና በቅንጅት እንዲሰሩ ያደርጋል፡፡

፪/ የኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚ፣ አስተዳዳሪ፣ ድርጅት ወይም የሥራ ኃላፊ የፈቃድ መስፈርት መጣሱን ያወቀ ወይም ሌላ ምርመራ የጀመረ አግባብ ያለው አካል ጥሰቱን ወይም የጀመረውን ምርመራ በተመለከተ ኮሚሽኑን ወዲያውኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

3/ A person who wants to transfer his rights pursuant to sub-article (2) of this Article shall secure approval of the Commission before effecting transfer.

**34. Exemption from Tax on Salary**

Foreign nationals employed by an industrial park enterprise that has undertaken to export its produce shall be exempted from paying income tax on their salary during five consecutive years starting from the date on which the enterprise obtained business license.

**35. Tripartite Committee**

1/ A tripartite committee consisting of the Ministry of Labour and Social Affairs, the Ministry of Industry, industrial park developer, operator or enterprise and employees' representatives shall be established in a park.

2/ The tripartite committee shall be responsible for:

a) ensuring the rights and duties of workers are respected and creating conducive conditions to prevent conflict through continuous consultation and engagement;

b) ascertaining, in consultation with the Ministry of Industry, that transfer of knowledge, skill and technology takes place and productivity increases;

c) Carrying out other activities that help attain industrial peace.

3/ The Commission shall, in consultation with the Ministry of Industry, follow up and provide assistance that the Committee discharges the responsibilities entrusted to it under sub-article (2) of this Article; the Commission shall also regulate the activities of the Committee.

**36.Law Enforcement and Exchange of Information**

1/ The Commission shall cause cooperation and coordination of appropriate security and law enforcement bodies operate within industrial parks with that of the industrial park developer, operator or enterprise.

2/ Where a law enforcement organ or any another relevant body comes to know of violation of the terms of permit by an industrial park developer, operator, enterprise or manager or any other organ that initiates any investigation into such matters, shall forthwith inform the Commission about such violation or commencement of investigations.

www.chilot.me

**፴፯. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

፩/ አግባብ ባላቸው ሌሎች ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ ደንብ ከጸናበት ቀን በፊት የተሰየመን የኢንዱስትሪ ፓርክ በተመለከተ ከኢንዱስትሪ ፓርክ አልሚዎች፣ አስተዳዳሪዎች እና ድርጅቶች ጋር የተፈጸሙ የመግባቢያ ስምምነቶችና የተሰጡ ውሳኔዎች ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

፪/ በዚህ ደንብ ለኢንዱስትሪ ፓርክ ተጠቃሚ የተሻለ መብት የሚሰጡ ድንጋጌዎች ከዚህ ደንብ መውጣት በፊት በተሰየመ የኢንዱስትሪ ፓርክ ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**፴፰ .መመሪያ ስለማውጣት**

፩/ ኮሚሽኑ የኢንዱስትሪ ፓርክ አሰያየም፣ ፈቃድ፣ ግንባታ፣ አስተዳደር፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎት፣ ቪዛና የመኖሪያ ፈቃድ፣ ጉምሩክ፣ የወጪ ንግድ፣ ቅሬታ አፈታት እና ሌሎች ከኢንዱስትሪ ፓርክ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ላይ ከቅርብ ባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር ረቂቅ መመሪያዎችን አዘጋጅቶ በቦርዱ ያጸድቃል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ቦርዱ የሚያወጣቸውን መመሪያዎች ለመተግበር የሚያስችሉ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያዎች ኮሚሽኑ ወይም የሚመለከተው መንግሥታዊ ተቋም ማውጣት አለበት፣ ኮሚሽኑ በሚመለከተው መንግሥታዊ ተቋም ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ መውጣቱን ይከታተላል፣ ያስተባብራል፡፡

**፴፱.ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረኑ ደንቦች፣ መመርያዎች እና አሰራሮች በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

**፵.ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መስከረም ፭ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**37.Transitory Provisions**

1/ Without prejudice to the provisions of other appropriate laws, memorandums of understanding concluded with industrial park developers, operators and enterprises and decisions taken as concerns industrial parks designated before the coming into force of these Regulations shall continue to apply.

2/ Provisions of this Regulation that confer better rights on industrial park end-users shall be applicable to industrial parks designated before the coming into force of this Regulation.

**38. Issuance of Directives**

1/ The Commission shall, in consultation with stakeholders draft directives, concerning: designation of industrial park, permit, construction, operation, one-stop shop service, visa and residence permit, customs, export trade, complaint handling and dispute resolution and other matters of relevance to industrial park cause them to be approved by the Board.

2/ The Commission or other pertinent governmental institutions shall issue detailed implementation directives enabling the enforcement of the directives issued by the Board pursuant to sub-article (1) of this Article. The Commission shall follow-up and coordinates the issuance of such directives by the appropriate governmental institutions.

**39. Inapplicable Laws**

No regulation, directive and practice shall, in so far as it is inconsistent with this Regulation, have force or effect with respect to matters covered by this Regulation.

**40. Entry into Force**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this September, 15th day of 2017.**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

www.chilot.me

www.chilot.me

www.chilot.me

www.chilot.me